# በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# የከተማ ልማት ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ

## በ12 የትግራይ ከተሞች የሚካሄደውን

## "የራስ አገዝ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ሕብረትሥራ ማህበር"

## ማስፈጸሚያ ማንዋል

ታህሳስ 2009 ዓ.ም

መቐለ

## መግቢያ

መንግስት የዜጐች የመኖሪያ ቤቶች አቅርቦትን ተግባራዊ ለማድረግ የከተማ ቦታ በሊዝ ለመስጠት በወጣ አዋጅ ቁጥር 721/2004 በምደባ የሚፈቀዱ ቦታዎችን አንቀፅ 12 ባስቀመጠው ድንጋጌ መሰረት በራስ አገዝ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ሕ/ሥ/ማህበር ለማካሄድ ሂደቱ ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለው ሁኔታ ለመሥራት በመንግስት በተቀመጡ የአፈፃፀም አቅጣጫ መሰረት ተግባራዊ እንዲሆን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በዚህ መመሪያ ተጠቃሚ ለመሆን ለሚፈልግ የከተማ ነዋሪ ከገቢው እየቆጠበ የመኖሪያ ቤት ችግሩን መቅረፍ እንዲችል ምዝገባው ቁጠባ መሰረት ያደረገ እንዲሆን ስለታመነበት፣

በሁሉም ትላልቅ የትግራይ ከተሞች የሚኖሩ የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች እንዲደራጁ ለምዝገባ በሚቀርቡበት ጊዜ ሊያሟሏቸው የሚገቡ ቅድመ-ሁኔታዎች አስቀድመው እንዲያውቁ በማድረግ በራስ አገዝ የጋራ የመኖሪያ ቤቶች የሚካሄደው የመኖሪያ ቤቶች ፕሮግራም ሕ/ሰቡ ከሚያደርገው ጥረት በተጨማሪ በመንግስት በሚደረግ ድጋፍ የመኖሪያ ቤት ባለቤት እንዲሆን በማድረግ ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር አስፈላጊ በመሆኑ፣

የከተማ ልማት፣ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሥራ አስፈፃሚ ም/ቤት መመሪያ እንዲያወጣ በሰጠው ስልጣን መሰረት መመሪያ ቁጥር 3/2009 አውጥቷል፣

## ክፍል አንድ

## የራስ አገዝ መኖሪያ ቤቶች ማህበር አደረጃጀትና የቦታ አሰጣጥ

ሀ. የአደረጃጀት አፈፃፀም ሥነ ስርዓት በሚመለከት፣

በዚሁ የራስ አገዝ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ሊደራጁ የሚችሉ የቤት ፈላጊዎች፡-

- የከተማው ነዋሪዎች፣
- በከተማው የሚኖሩ በመንግስት መ/ቤቶች የሚያገለግሉ ቋሚ የመንግስት ሠራተኞች፣
- በከተማው የሚኖሩ የልማት ተቋማትና ሕዝባዊ ማህበራት የሚያገለግሉ ቋሚ ሠራተኞች፣
- የአገር መከላከያ ሠራዊት አባላት የሆኑ የትግራይ ተወላጆች፣
- በፌዴራል አዲስ አበባና ድሬደዋ የሚገኙ የፖሊስ አባላት ፣
- የትግራይ ክልል ልዩ ኃይል አባላት፣
- ዳያስፖራ የትግራይ ተወላጆች

ለ. በዚሁ የራስ አገዝ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ለመደራጀት የሚኖር ቅድመ ሁኔታ፣

1. የከተማው ነዋሪዎች፣

- ሁለት ዓመት እና በላይ በከተማው ነዋሪ የሆኑና ኗሪነታቸው በመታወቂያ ወረቀት ማረጋገጥ የሚችሉ፣ መታወቂያው የተሰጠበት እና የታደሰበት ቀን በግልፅ የሚያሳይ ሆኖ ለምዝገባ ሲቀርብ በከተማው ለሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ ስለመኖሩ የሚያሳይ መሆን አለበት፣
- የከተማ ነዋሪዎች ከመታወቂያ ወረቀት ውጪ ሌላ የድጋፍ ወረቀት በማቀረብ መደራጀት አይቻልም፡፡ በሚደራጅበት ከተማ ኗሪ ሆኖ ነገር ግን በከባድ ሕመም ምክንያት ከከተማው ውጪ የቆየ፣ ለስንት ጊዜ እንደቆየና እንደሚቆይ ህጋዊ የሕክምና ማስረጃ ካቀረበ ለመደራጀት ብቁ ይሆናል፣
- ቋሚና ተከታታይ ገቢ ያለውና ለገቢው ግብር የሚከፍል መሆኑ ማረጋገጫ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፣
- የተደራጀው ሰው በራሱ ወይም በባለቤቱ በሚደራጅበት ከተማ መኖሪያ ቤት ወይም ቦታ የሌለው የጋራ መኖሪያ ቤት/ኮንድሚኒየም የሌለው መሆን አለበት፣
- በውርስ ወይም ስጦታ የተገኘ ከአንድ ሰው በላይ የሚያስተዳድሩት ቤት እና ቦታ ካለ የቦታው ስፋት ከከተማው ስታንዳርድ በታች ከሆነ ሊደራጅ ይችላል፣

- ከተደራጀ በኋላ ከስታንዳርድ በታች ስለመሆነ ከማዘጋጃ ቤት ወይም ከቦታ ማልማትና ማኔጅመንት የሥራ ሂደት ማረጋገጫ ያቀርባል፣
- ይዞታው ከስታንዳርድ በላይ ሆኖ ከተገኘ ማህበሩ ይፈርሳል፣

## 2. የመንግስት ወይም የልማትና የህዝባዊ ማህበሮች ቋሚ ሠራተኞች፡-

- የመንግስት ሠራተኛ ወይም የልማትና የሕዝባዊ ማህበሮች ቋሚ ሠራተኞች ከሆኑ ከተቋሙ ቋሚ ሠራተኛ መሆኑንና ወርሃዊ የሚከፈለው ደመወዝ የሚገልፅ ደብዳቤ ከተቋሙ የሰው ሃብት አስተዳደር ተረጋግጦ በከፍተኛ ሃላፊ የተፈረመ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት፣
- በከተማው ነዋሪ የሆነ የመንግስታዊ ወይም የልማትና የህዝባዊ ማህበራት ቋሚ ሰራተኛ የሆነ የመታወቂያ ወረቀት ማቅረብ ወይም በከተማው 2 ዓመትና በላይ ኗሪ መሆኑ የማረጋገጥ ግዴታ የለበትም፣
- በሚደራጅበት ከተማ የሚገኘው ተቋም ሰራተኛ ሆኖ ነገር ግን በትምህርት ወይም በሕክምና ምክንያት ከከተማው ውጪ የሆነ ከሆነ ሕጋዊ ማስረጃ በማቅረብ ከመ/ቤቱ ያልተሰናበተ መሆኑ ማረጋገጫ ካቀረበ ለመደራጀት ብቁ ይሆናል፣
- ማዕከላቸው በከተማዋ የሆኑ የፌዴራል፣ ክልል፣ ዞንና ወረዳ የመንግስት የልማትና የህዝባዊ ማህበራት የሚያገለግሉ ሠራተኞች በቋሚነት በከተማዋ እንዲሰሩ የተመደቡ መሆናቸው ከሚከፈላቸው ወርሃዊ ደመወዝ ጋር ከዋና የተቋሙ ሃላፊ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ አለባቸው፣
- የሚደራጀው ሰው በራሱ ወይም በባለቤቱ ስም በሚደራጅበት ከተማ የመኖሪያ ቤት፣ ወይም ቦታ ወይም የጋራ መኖሪያ ቤት/ ኮንዶሚኒየም የሌለው መሆን አለበት፣

## 3. ከአገር መከላከያ፣ የፌዴራል ፖሊስ ሠራዊት እና ከልዩ ኃይል እንዲሁም ከአዲስ አበባና ድሬደዋ ሕዝባዊ ፖሊስ የሚያገለግሉ የትግራይ ተወላጆች፣

- የአገር መከላከያ፣ የፌዴራል ፖሊስና የልዩ ኃይል እንዲሁም በአዲስ አበባና ድሬደዋ ሕዝባዊ አባላት የሆኑ ተወላጆች አባላት ስለመሆናቸው፣ በሥራ ላይ የሚገኙ ስለመሆናቸው ከሚከፈላቸው የወር ደመወዝ ጋር የሚገልፅ ማስረጃ ከሚመለከተው የበላይ ሃላፊ ተፈርሞ ለሚደራጅበት ከተማ በአድራሻው የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት፣
- የአገር መከላከያ፣ የፌዴራል ፖሊስ ሰራዊትና የልዩ ሃይል እንዲሁም የአዲስ አበባና ድሬደዋ ሕዝባዊ ፖሊስ አባላት ሊብቻቸው ወይም ከልዝቡ ጋር ሊደራጁ የሚችሉ ሲሆን፣

- የአገር መከላከያ፣ የፌዴራል ፖሊስና የልዩ ኃይል እንዲሁም በአዲስ አበባና ድሬደዋ ሕዝባዊ አባላት በራስ አገዝ የጋራ መኖሪያ ቤት ማህበር ለመደራጀት በሁሉም የትግራይ ከተሞት ውስጥ በራሱ ወይም በባለቤቱ ስም የሚተዳደር መኖሪያ ቤት የሌለው መሆኑ ውል መፈጸም አለበት፣
- የአገር መከላከያ፣ የፌዴራል ፖሊስና የልዩ ኃይል እንዲሁም በአዲስ አበባና ድሬደዋ ሕዝባዊ አባላት በመረጡት አንድ የትግራይ ከተማ ብቻ የመደራጀት መብት ይኖራቸዋል፣

4. **በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ተደራጅተው የከተማ የቤት መሥሪያ ቦታ የሚያገኙበት አግባብ፣ የዳያስፖራ የመኖሪያ ቤቶች ሕ/ስ/ማ አደረጃጀትና የሚያደራጀው አካል፣**

- የዳያስፖራ የራስ አገዝ የመኖሪያ ቤቶች የህብረት ሥራ ማህበር የሚደራጁት በኤምባሲዎችና ሚስዮኖች በኩል ይሆናል፣
- የዳያስፖራ የራስ አገዝ የመኖሪያ ቤት የሚደራጁ በውጭ ጉዳይ ሚ/ር የዳያስፖራ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ደብዳቤ ማቅረብ አለባቸው፣
- በዚህ የመኖሪያ ቤቶች ልማት ተጠቃሚ የሚሆኑ ማህበራት መሬት ለመረከብ ለግንባታ የሚያስፈልገውን አጠቃላይ ወጪ በዝግ የባንክ ሒሣብ በውጭ ምንዛሪ ማስቀመጣቸው ማረጋገጫ ሲያቀርቡ ይሆናል፣
- በዚህ ፕሮግራም ተጠቃሚ የሚሆን ዳያስፖራ በትግራይ ከሚገኙ ከተሞች በመረጡት አንድ ከተማ ሆኖ ከዚህ በፊት መኖሪያ ቤት የሌለው መሆን አለበት፣

## ሐ. የአደረጃጀት ቅደም ተከተል፣

የመኖሪያ ቤት ሕ/ስ/ማ/ አባል ለመሆን የሚፈልግ ሰው በመመሪያ ቁጥር 3/2009 የተደነገገውን በሚሟላት በሚከተሉት አግባቦች መደራጀት አለባቸው፣

1. **ለመደራጀት ብቁ የሚያደርግ ገንዘብ በዝግ ሂሣብ ገቢ ማድረግ፣**

- የማህበሩ አባላት ከባንክ ጋር ትስስር ሣያደርጉ የግንባታው ግምት 50% ገቢ ሊያደርጉ የሚችሉ ከሆነ በባንክ/ ማይክሮፋይናንስ በዝግ ሂሣብ በማህበሩ ስም መቆጠብ አለባቸው፣
- ከባንክ ጋር ትስስር ያደረጉ ማህበራት እያንዳንዱ አባል ከጠቅላላው የግንባታ ዋጋ 20% በማክሮፋይናንስ ማህበሩ በወከላቸው አባላት በኩል በዝግ አካውንት ተቀማጭ ማድረግ አለባቸው፣
- በወኪሎቻቸው በኩል የሚቆጥቡ አባላት ወኪሎቻቸው በዝርዝር መርጠው መፈረም አለባቸው፣

2. ወደ የሚያደራጀው አካል መቅረብና መደራጀት

መሟላት ያለባቸው ማስረጃዎች፡-

- በነዋሪነት የሚደራጅ ከሆነ የታደሰ የመታወቂያ ካርድ ኦሪጅናልና የማይመለስ 3 ኮፒዎች፣
- እንዲሁም ቋሚ ወይም ተከታታይ ገቢ ያለው ስለመሆኑ የፅሁፍ ማስረጃ የሚያቀርብ፣
  - ነጋዴ ከሆነ የሒሣብ መዝገብና ግብር የከፈለበት ሕጋዊ ደረሰኝ ማቅረብ አለባቸው፣ የሒሣብ መዝገብ ማቅረብ ግዴታ የሌለባቸው ነጋዴዎች መንግስታዊ ግብር የከፈሉበት ሕጋዊ ደረሰኝ ማቅረብ አለባቸው፣
  - የኮንትራት ሠራተኞች ከሆኑ በመንግስታዊ፣ ሕዝባዊ ማህበር እና የልማት ተቋማት የሚሰሩ ከሆነ ወርሃዊ ደመወዛቸው የሚገልፅ የተቋሙ የድጋፍ ደብዳቤ፣ በግል ተቋማት የሚሰራ ከሆነ/ከሆነች የሚቀርበው የወርሃዊ ገቢ ደብዳቤ የመነግስት ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፣
  - ጡረተኛ ከሆነ ጡረተኛ ስለመሆኑና ገቢያቸውን የሚያረጋገጥ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፣
  - የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋም ከሆነ ሕጋዊ የተደራጀበትና፣ የሚሰራበትና ገቢውን የሚገልፅ ማስረጃ በማህበሩ ወይም በግል ተቋሙ ስም ከሚከፍልበት የግብር ደረሰኝ ጋር ማቅረብ አለበት፡፡ በህግ ግብር የማይከፍሉ የሲድማኒ ማጠራቀሚያ ካፒታል የተደራጁ የልማት ቡድን የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋም ካሉ ማረጋገጫ ሰርትፊኬት ያቀርባሉ፣
  - አላይ ከተጠቀሱት ውጭ የሚገኙ የሕህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰሩበት እና ገቢያቸውን የሚገልፅ እና ለገቢያቸው የከፈሉበት የመንግስት ግብር ማስረጃ ማቅረብ፣
- የሚደራጅ ሰው ቋሚ ገቢው፣ በባለቤቱ በኩል ከሆነ ሕጋዊ የፅሁፍ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፣
- በመንግስት ሰራተኛ ወይም በልማት ተቋማት ሠራተኛ ወይም በሕዝባዊ ማህበራት ቋሚ ሰራተኛ የሚደራጅ ከሆነ ቋሚ ሠራተኛ ስለመሆኑ፣ የደመወዝ መጠን የሚገልፅ ማረጋገጫ የድጋፍ ደብዳቤ፣
- የአገር መከላከያ፣ የፌዴራል ፖሊስና የልዩ ኃይል እንዲሁም በአዲስ አበባና ድሬደዋ ሕዝባዊ አባል መሆኑና ወርሐዊ የደመወዝ መጠን የሚገልፅ ለአደራጁ አካል በተፃፈ የድጋፍ ደብዳቤ ፣
- ትዳር ያለው ከሆነ የባለቤቱ ማንነት የሚገልፅ ማስረጃ የኗሪነት፣ የሥራ መታወቂያ ካርድ ወይም ሌላ ማስረጃ ኦሪጅናል ከማይመለስ አንድ ኮፒ ጋር፣
- ትዳር የሌለው ከሆነ ትዳር እንደሌለው የሚያረገግጥ ማስረጃ ከማህበራዊ ፍ/ቤት የሚያቀርብ፣

- በትምህርት ምክንያት ከከተማው ውጭ የሚኖሩ ቋሚ ሠራተኞች ወይም በሕመም ምክንያት ከከተማው የወጣ ኗሪ የቋሚ ገቢው መጠን የሚገልፅ የድጋፍ ደብዳቤ የሚያቀርብ፣ የማህበሩ አባላት በዝግ አካውንት ገቢ ያደረጉበት ማረጋገጫ ሰነድ/ደብዳቤ ከአባላት ስም ዝርዝር ጋር፣
- በሦስት ኮፒ የተዘጋጀ የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ፣ የእያንዳንዱ አባል ሦስት ፓስፖርት መጠን ያለው ፎቶግራፍ ማቅረብ አለበት፣
- በእያንዳንዱ አባል ስም በህግ ቀርቦ ተቀባይነት ያለው የመመዝገቢያ ማመልከቻ ቅፅ 001 በሶስት ኮፒ በማቅረብ በአካል ቀርቦ ቃለመሃላ መፈጸም አለበት፣

## እውቅና ስለማግኘት፣

- እያንዳንዱ የማህበሩ አባል እላይ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች በመያዝ ወደ ሚደራጁበት ከተማ የሚገኝ የፍትህ ቢሮ/ ጽ/ቤት በአካል ቀርቦ ውል ይፈፀማል፣
- የአገር መከላከያ፣ የፌዴራል ፖሊስና የልዩ ኃይል እንዲሁም በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ሕዝባዊ፣ በትምህርት ወይም ልዩ ባህርይ ያለው ሥራ የተሰማሩ አካላትና በከባድ ሕመም ምክንያት ከከተማው ውጪ በሚገኝ የሕክምና ተቋም የሚገኙ መሆናቸው ማስረጃ ያቀረቡ ካልሆነ በስተቀር በውክልና መመዝገብ አይቻልም፣
- እያንዳንዱ የተመሰረተ ማህበር የራሱ የሆነ ፋይልና የባህር መዝገብ ይኖረዋል፣
- ከመቀሌ ውጪ በሚገኙ ከተሞች የሚደራጁ ማህበራት ከመሬት ልማትና ማኔጅመንት የሥራ ሂደት በራሱ ስም ወይም በትዳር ባለቤቱ ስም የመኖሪያ ቤት የሌለው ስለመሆኑ በግል ወይም በጋራ ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፣
- በመቀሌ ከተማ የሚደራጅ በከተማው በራሱ/በባለቤቱ ስም የመኖሪያ ቤት የሌለው ሰለመሆኑ በህግ ቀርቦ ተቀባይነት ያለው የውል ቃለመሃላ በፍትህ ቢሮ/ጽ/ቤት በመቅረብ እንዲፈርም ይደረጋል፣
- የአባላት ብዛት ከ20 የሚያንስ ወይም የሚበልጥ ከሆነ ወይም ከአባላት ውስጥ አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ ሣያሟላ የሚቀር ሰው ካለ ማህበሩ እውቅና አያገኝም፣
- የፍትህ ቢሮ/ጽ/ቤት ወይም ማዘጋጃ ቤት እንዲደራጁ የተመዘገቡት በአንድ ማህበር ውስጥ ያሉ አባላት ዝርዝር ለተጨማሪ ማስረጃ/ጥቆማ ሊለጥፋቸው ይችላል።
- እያንዳንዱ ማህበር ከተደራጀበት ጊዜ ጀምሮ ለ10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ምዝገባው ሕዝብ እንዲያውቀው እና አስፈላጊውን ማስረጃዎች እንዲሰጥ የመረጃ ምንጮች ጋዜጣ ወይም በሌሎች

የአካባቢው የብዙሃን መገናኛ ማዕከሎች በየከ/ከተማው/ቀበሌዎች፣ ሕዝብ በብዛት በሚሰበሰብበት አደባባዮች ሊገለፅ ይችላል፣

- ማንኛውም ሰው ከአንድ ጊዜ በላይ ተደራጅቶ ከተገኘ ከሁሉም ምዝገባዎች እንዲሰረዝ ይደረጋል፣
- ማንኛውም ሰው ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ያቀረበው ማስረጃ ወይም የሞላው ቅፅ የተሣሣተ ወይም ሐሰተኛ ሆኖ ከተገኘ በህግ እንዲጠየቅ ከማድረግ በተጨማሪ ከማህበሩ እንዲሰረዝ ይደረጋል፣
- ሁሉም ማስረጃዎች አሟልተው የተደራጁ አካላት የመኖሪያ ቤት ሕ/ስ/ማህበር በፍትህ ቢሮ/ጽ/ቤት ሰርትፊኬት ይሰጣቸዋል፣
- የህንፃው ግንባታ ጠቅላላ ግምት 50% ያጠራቀመ አካል በማህበሩ ስም እንዲያስቀምጥ፣ 20% ያጠራቀመ ደግሞ ተጨማሪ 30% እና ከዚያ በላይ ባንኩ ወይም ማይክሮፋይናንሱ ያበደራቸው መሆኑ የድጋፍ ደብዳቤ ይይዛሉ፣
- እያንዳንዱ ማህበር የጠቅላላ አባላት ተሰልቶ በመመሪያው የተቀመጠውን ለማካካሻ ወጪ የሚሆን በመቀሌ እያንዳንዱ 5000፣ በሌሎች ከተሞች ለእያንዳንዱ 4000 ወደ መንግስት ገቢ እንዲያደርጉ ሲገለፅላቸው ገቢ ያደርጋሉ፣

## የምዝገባ ቦታ፣

- እውቅና ያገኘ ማህበር የሚከተሉትን ማስረጃዎች በመያዝ ወደ ማዘጋጃ ቤት በመሄድ መመዝገብ ይችላል፣
  - ማህበሩ እውቅና ያገኘበት ሰርትፊኬት ዋናውን የማይመለስ አንድ ኮፒ፣
  - የፀደቀ የማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ ዋናው፣
  - በማህበሩ ስም በዝግ ሒሣብ ገቢ የተደረገበት ማስረጃ፣
  - ባንክ ወይም የማይክሮፋይናንስ ተቋም ለማህበሩ ብድር የሰጠው መሆኑ ማረጋገጫ የሰጠበት የብድር ስምምነት ድጋፍ፣
  - ለካሣ ገቢ እንዲያደርጉ ሲጠየቁ የከፈሉበት የገቢ ደረሰኝ ኦሪጂናል ከማይመለስ አንድ ኮፒ፣
  - በአጠቃላይ አደራጁ አካል ያፀደቃቸው ማስረጃዎች ያቀርባል።
- ከዚህ በላይ በዝርዝር የተገለፁት ማስረጃዎችና ድጋፎች በመያዝ በማዘጋጃ ቤት ምዝገባ ይካሄዳል፣
- ማዘጋጃ ቤቱ ማስረጃቸውን አሟልተው የቀረቡትን ማህበራት እንደየመጡበት ቅደም ተከተል የያንዳንዱ መዝገብ በመክፈት በባህረ መዝገብ ያሳርፋል፣
- አሟልተው ያልቀረቡ ማህበራት ግን አሟልተው እስካቀረቡ በቅድመትነት እና በቅደም ተከተል ሊመዘገቡ አይችሉም፣

## ቦታ የሚፈቀድበት አግባብ/ ውሣኔ መስጠት

- አስፈላጊውን ዝርዝር ማስረጃ አሟልተው የቀረቡ ማህበራት ባቀረበው ዝርዝር መሰረት ቦታ እንዲፈቀድላቸው በማዘጋጃ ቤቱ ሸኚነት ወደ ከተማው ካብኔ እንዲላክ ይደረጋል፣
- ማስረጃቸው አጠናቀው/ አሟልተው ያላቀረቡ ማህበራት ለውሣኔ ወደ ከተማው ካብኔ መላክ አይቻልም፣
- የከተማው ካብኔ ለቀረቡለት የማህበራት ዝርዝር በማየት ውሣኔ በመስጠት ለማዘጋጃ ቤቱ/ለከተማ ልማት፣ ንግድና ኢንዱስትሪ ጽ/ቤት እንዲላክ ያደርጋል፣

## የቦታ አሰጣጥ አግባብ

- በየጊዜው በከተማው ካብኔ ውሣኔ ተሰጥቶባቸው ወደ ማዘጋጃ ቤት/ለከተማ ልማት፣ ንግድና ኢንዱስትሪ ጽ/ቤት የተላኩ ማህበራት በመመሪያው መሠረት የቦታ አሰጣጥ ሂደት ይስተናገዳል፣
- ለነዚህ ዓላማ ተብሎ የተዘጋጀ መሬት ለእያንዳንዱ ብሎክ የራሱ የሆነ ልዩ መለያ ቁጥር እንዲሰጠው ይደረጋል፣
- የተዘጋጀው መሬት በህጋዊ ደብዳቤ የሣይቱ መለያ ቁጥር በማድረግ ገላጭ በሆነ መንገድ ይዘጋጃል፣
- የተዘጋጀው መሬትና የቀረቡ ማህበራት ቁጥራቸው እኩል ካለሆነ ወይም የተዘጋጀው መሬት ከማህበራቱ ቁጥር የሚበልጥ ከሆነ ለሚደርሳቸው ቦታ/ብሎክ ቁጥር በእጣ እንዲለዩ ይደረጋል፣
- የተዘጋጀው የፕሎት/ብሎክ ቁጥር ከተደራጁት ማህበራት ቁጥር የሚያንስ ከሆነ ግን ለሴቶችና አካል ጉዳተኞች የቤተሰብ መሪዎች 30% እና ከዛ በላይ የያዙ ማህበራት ቅደሚያ እንዲስተናገዱ በማድረግ የቀሩት በዕጣ እንዲለዩ ይደረጋል፣
- ቀደም ሲል በተዘጋጀው የቦታ አሰጣጥ ያልተስተናገዱ ማህበራት ካሉ በቀጣይ በሚዘጋጅ የቦታ አሰጣጥ ቅድሚያ ወይም ቀጥታ ለብቻቸው ዕጣ እንዲወጣላቸው ይደረጋል፣
- የዕጣ አሰጣጥ ሂደቱ አግባብነት ባለው ቃለ-ጉባኤ በመያዝ ከማዘጋጃ ቤቶች፣ የቤቶች ልማት ኤጀንሲ እና ከእያንዳንዱ ዕጣ የሚወጣላቸው ማህበራት የተወከሉ አንድ አንድ ሰው በተገኙበት ይካሄዳል፣
- ያልወከሉ ማህበራት ቢኖሩም የዕጣ አወጣጥ ስነ ስርዓቱ ግን ሊቀጥል ይችላል፣
- የኮሚቴው ሰብሳቢ ከማዘጋጃ ቤት የተወከለ ፀሐፊ ከቤቶች ልማት ኤጀንሲ የተወከሉ የተቀሩት አባላት በመሆን የእጣ አወጣጥ ሥራ ይከናወናል፣

## የቦታ አሰጣጥ ቅደም ተከተል

- ዕጣ የወጣላቸው ማህበራት ዝርዝራቸው ለመሬት ልማትና ማኔጅመንት የሥራ ሂደት ገቢ ይደረጋል፣
- በደረሣቸው ፕሎት/ብሎክ ቁጥር መሰረት የተፈቀደላቸው ቦታ የግንባታ ውል በመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቀርበው እንዲፈርሙ ይደረጋል፣
- ማህበሩን በመወከል የሚፈፅሙት አካላት በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የተሾሙ አካላት ይሆናል፣
- ውል ያሰሩ ማህበራት ውል ያሰሩበትን ፕሎት/ብሎክ የሚገልፅ ማረጋገጫ የጋራ ሣይት ፕላን በማህበሩ ስም ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው ይደረጋል፣

⇒ የሚሰጠው የጋራ ሣይት ፕላን ለቦታው በዚህ መመሪያ መሰረት የተፈቀደ መሆኑ የሚያሳይ ርእስ የማህበሩ ስም ስፋት፣ አዋሣኝ፣ ፕሎት/ብሎክ ቁጥር አመላካች አቅጣጫዎች፣ ያካተተ በፕላነር ባለሙያ ተዘጋጅቶ በመሬት ልማትና ማኔጅመንት አስተባባሪ ፀድቆ እንዲሰጥ ይደረጋል፣

- ማዘጋጃ ቤት ውል የተፈጸመበት ቦታ በ15 ቀናት ውስጥ ለማህበሩ ማስረከብ አለበት፣
- በእያንዳንዱ ማህበር የተዘጋጀ የቤት ዲዛይን Typology መርጠው ቦታ ከተረከቡበት በ15 ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለባቸው፣
- ማንኛውም ማህበር የመረጠው የህንፃ ዲዛይን በማህበሩ ስም በማዘጋጃ ቤት ወይም የመሬት ማልማትና ማኔጅመንት ማታም ሲደረግበት ግንባታ ማካሄድ አለባቸው፣
- የራሣቸው ዲዛይን የሚያቀርቡ ማህበራት ዲዛይናቸው በዚህ መመሪያ መሰረት የተዘጋጀ መሆኑ ተረጋግጦ ወደ ክ/ል/ን/ ኢንዱስትሪ ቢሮ ወይም ቢሮው ወደወከለው ተቋም ውል ከፈፀሙበት በአንድ ወር ውስጥ ተቀባይነት ካገኘ እንዲቀጥሉ ይደረጋል፣
- የቀረቡት ታይፖሎጂ ዲዛይኖች ዝርዝር ፕላን እንደየከተማው ሁኔታ ከዲዛይኑ ለውጥ ሣይደረግበት በኤሌክትሪካል፣ ተፋሰስና ቁመት እና መዋቅሮች ሊሰራለት ይችላል፣
- የክ/ል/ን/ኢንዱስትሪ ቢሮ ተጨማሪ አማራጭ ታይፖሎጂዎች ሊልክ ይችላል፣
- የግንባታ መጀመሪያ እና መጨረሻ ጊዜ በደንብ ቁጥር 76/2005 በተቀመጠው ጊዜ መሰረት ሆኖ ማህበሩ ዲዛይን መርጦ ካፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ ይሆናል፣
- ከባንክ ወይም ማይክሮፋይናንስ ተቋም ትስስር የፈጠሩ ማህበራት ከሆኑ የተሰጣቸው ሣይት ፕላን እና የቤት ፕላን ስምምነት በባንኩ ስም እንዲመዘገብ/እንዲታገድ ይደረጋል፣

## ክፍል 2

# ቦታ ማዘጋጀት፣ ሕንጻ መገንባት፣ ከዝግ ሒሳብ ገንዘብ መልቀቅ፣ የግል ካርታ ማስረከብ

### ሀ. ቦታ ማዘጋጀት

- ከተሞች ለዚሁ የራስ አገዝ የመኖሪያ ቤቶች የሚውል በቂ መሬት በመምረጥ ማዘጋጀት አለባቸው
- የመረጣ ሂደቱ ያካባቢውን ሕብረተ ሰብያሳተፈ የከተማ ፕላን የተከተለ ለቤቶች ማህበር ግንባታአቀማመጥ የተመቹ መሆን አለበት።
- ለዚህ ዓላማ የተዘጋጀ መሬት የሚገኝ አካባቢ በመዋቅራዊ ፕላኑ በተቀመጡ የዋና ዋና መንገዶች እና ሌሎች የጋራ ማህበራዊ አገልግሎቶች ወጪዎች አካባቢው በድጋሚ በነዚህ የማህበር ሰፋት መሰረት መሸንሸን።
- የሚሸነሸነው መሬት በመቀሌ አላማጣ ኮረም ማይጨው ዓቢይዓዲ ውቅሮ ዓዲግራት ዓድዋ አክሱም ሽረ እንዳስላሴ የሚሰጥ ህንፃ የሚያርፈው የጋራ ህንፃ ስፋት ለአንድ 20(ሃያ) አባላት የያዘ ማህበር የሚሰጥ ህንፃ የሚያርፈው ብቻ የቦታ ስፋት 1400(አንድ ሺህ አራት መቶ) ካሬ ሜትር ሆኖ፤ እያንዳንዱ ብሎክ የጋራ ህንፃ ከመንገድ (set back) ሁለት ሜትር ርቆ መገንባት አለበት።
- በሽራሮ እና ሁመራ ለአንድ 16( አስራ ስድስት) አባላት የያዘ ማህበር የሚፈቀድ ህንፃ ያረፈበት የጋራ ህንፃ የቦታ ስፋት 1600 ( አንድ ሺህ ስድስት መቶ ) ካሬ ሜትር ሆኖ፤ እያንዳንዱ ብሎክ የጋራ ህንፃ ከመንገዱ (set back) ሁለት ሜትር ርቆ መገንባት አለበት።
- በህንፃውና በመንገድ መካከል ያለው 2 ሜትር (set back) ከጋራ ህንፃ የሚያርፍበት ቦታ (1400 ካሬ ሜትር) ስፋት ውጪ ይሆናል።

### ለ. የሚዘጋጀው የሰፈር ፕላን

- ከተሞች ለዚህ ዓላማ የሚውል ቦታ መርጠው ለሚገነቡት ብሎኬት አቀማመጥና የቦታ ልማት ዲዛይን በሚዘጋጀው የሰፈር ፕላን በተስተናጋጅ ብዛት መሰረት ለአካባቢው የሚያስፈልግ የማህበራዊ አገልግሎት፤ የአገልግሎት ማእከላትና የአረንጓዴ የህዝብ ቦታ ታሳቢ ማድረግ አለበት።

### ሐ. የሚገነባው ህንፃ ዓይነት በተመለከተ

- በሁሉም 12 የትግራይ ከተሞችበራስ አገዝ የጋራ መኖሪያ ቤቶች የሚገነባው ህንፃ ባለ አንድ ፎቅ (Modern Town House) ይሆናል።
- በአንድ ማህበር የሚገኙ አባላት እያንዳንዳቸው በመሬትና ላይኛው ፎቅ የራሳቸው ቤት ይኖራቸዋል።

- የሚሰራው ህንፃ ለእያንዳንዱ ማህበር የሚኖረው የመኖሪያ አገልግሎት በታችኛው ክፍል (Ground Floor) ሳሎን እና መመገቢያ፤ኩሽና ሽንትቤትና ደረጃዎች ያጠቃለለ ሲሆን በላይኛው (Upper Floor) ሶስት መኝታ ቤቶችና ሽንትቤት ይኖረዋል።
- በአንድ ማህበር የሚኖረው መዋቅር ይሁን መውጫ ገፅታ ማለት ቀለምንና አጥርን ጨምሮ ሙሉ በሙሉ እስከሚጠናቀቅ በተናጠል መስራት አይፈቀድም።
- እያንዳንዱየማህበሩ አባል በህንፃው ይሁን በመሬት ህንፃው የሚያርፍበት የጋራ መጠቀሚያ  እኩል ድርሻ አለው።
- በአንድ ማህበር የሚኖረው መዋቀራዊ ይሁን ውጫዊ ገፅታው ሙሉ በሙሉ እስከሚጠናቀቅ ተመሳሳይ ዲዛይን ይኖረዋል።
- በአንድ ማህበርየ ሚኖረው መዋቅራዊ ይሁን ውጫዊ ገፅታ ቀለምና አጥር ጨምሮ ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይ ይሆናል።

መ. የህንፃው ግምት

- በ12 የትግራይ ከተሞች በዚህ የራስ አገዝ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ለአንድ አባል የሚደርሰው ቤት ለህንፃው መዋቅራዊ ስራዎች እና ውጪዊ ማጠናቀቂያ ጨምሮ ጠቅላላ ግምቱ ለእያንዳንዱ አባል የሚደርሳው 240,000.00(ሁለት መቶ አርባ ሺ ብር)ይሆናል።
- ከባንክ ብድር ሳይወስዱ የሚሰሩ ማህበራት እያንዳንዳቸው 20% በዝግ የባንክ ሂሳብ ቆጥበው ህጋዊ የራስ አገዝ የጋራ መኖሪያ ቤት ሕ/ስ/ማ መለያ (ሰርቲፊኬት)ማግኘት ፤እውቅና ካገኘ በኋላ ደግሞ 30% ጨምሮ በአጠቃላይ 50% ማለት 120 000 00(አንድ መቶ ሃያ ሺ ብር) በዝግ አካውንት ወይም በማይንቀሳቀስ መቆጠብ ከቻለ ለማህበሩ ቦተ ይሰጠዋል።
- ማህበሩ ከባንክ ወይም ከማይክሮ ፋይናንስ የብድር ትስስር የሚያደር ከሆነ መነሻ ካፒታል የአጠቃላይ ግምት 20% በባንክ መቆጠብ ከቻለና ተጨማሪ የብድር ስምምነት ከአጠቃላይ ግምት 50% የማያንስ እንደሚያበድረው ከባንክ /ማክሮፋይናንስ/ በማህበሩ ስም ገቢ የተደረገ ገንዘብ እንዳለ ማረጋገጫ ደብዳቤ ማቅረብ ከቻለ ቦታ ይሰጠዋል።
- በማህበሩ ስም በዝግ ባንክ የተቀመጠው የገንዘብ መጠን ማህበሩ በየጊዜው ወጪ  በማድረግ ወይም ከባንክ ጋር በማስተሳሰር ግንባታው የማጠናቀቅ ግዴታ አለበት።

ረ. የተቆጠበውን ገንዘብ ከዝግ ሂሳብ መልቀቅ በተመለከተ

- በዝግ ሂሳብ ከተቀመጠ ጠቅላላ የገንዘብ መጠን መልቀቅ የሚቻለው ቦታ ተረክበው ውል አስረው የግንባታ ፈቃድ ሲሰጣቸቸውአርባ ከመቶ (40%)፤የመሰረት ስራ ተጠናቆ የማህበሩ አጠቃላይ ዓምዶ/ችኮለኖች Columns)ሲጠናቀቅ አርባ በመቶ አጠቃላይ መዋቅርና የላይኛው መደምደሚያ ሲጠናቀቅ አስር ከመቶ(10%) እንዲሁም ውጫዊ ማጠቃለያ ግንባት ሲጠናቀቅ ቀሪው አስር በመቶ(10%) ይሆናል።
- ከባንክ ብድር የወሰዱ ማሕበራት መጀመሪያ ቦታ ሲረከቡ የሚለቀቅ የገንዘብ መጠን ከባንኩ ጋር ባደረጉት ስምምነት መሰረት ሁኖ፣ አስር በመቶ (10%) ግን የመዋቅር እና የውጫዊ ገጽታ ግንባታ ሲያጠናቅቁ የሚለቀቅ ይሆናል።

ሰ. የግል ካርታ መረከብ፣

- በራስ አገዝ የጋራ መኖሪያ ቤቶች የሚሰሩ ማህበራት ለእያንዳንዱ የማህበር አባል የቤት ክፍፍል የሚደረገው አጠቃላይ የመዋቅር (ኮለን) እና የላይኛው ቢም (ማሰሪያ) እንዲሁም የውጪ ገጽታ ግንባታ ሲጠናቀቅ ሁኖ፣ የቤት ክፍፍል ካደረጉ በኋላ የቤት ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ለእያንዳንዱ የማህበሩ አባል እንዲደርስ ሲደረግ፣ ብድር ያለው ከሆነ ግን ታግዶ እንዲቆይ ይደረጋል።
- ግንባታው ሲጠናቀቅ ከባንክ የብድር ትስስር ያላቸው ማህበራት የመለሱ መሆናቸው ወይም ብድሩ ወደ እያንዳንዱ ግለሰብ እንዲዛወር አበዳሪ ተቋም ባንክ/ ማይክሮፋይናንስ ማረጋገጥ አለበት።
- እያንዳንዱ የማህበሩ አባል የቤት ክፍፍል ካደረገ በኋላ የድርሻውን የውስጥ መከፋፈያ መገንባት የሚችል ሲሆን፣ ማህበሩ ግን በጋራ ደንብ የሚቀጥል ይሆናል።
- ማህበሩ ግንባታ ሲያጠናቅቅ ክፍፍል ማካሄድ በሚቻልበት ደረጃ መድረሱ በማዘጋጃቤት የመሬት አስተዳደር በኩል የፅሁፍ ማረጋገጫ ሲያገኙ በእጣ እንዲለይ ይደረጋል።
- ማንኛውም የማህበሩ አባል የግል ካረታ ከያዘ ከጋራ ዲዛይን ውጭ በግሉ ተጨማሪ ውጫዊ ግንባተ ማካሄድ አይችልም።
- በማህበር ተደራጅተው የመኖሪያቤት ለሚገነቡ የተሰጡ ቦታዎች ከሚታረስ መሬት ውጭ የተከፈለ ካለ የካሳና የመሰረተ ልማት ወጪዎች ብቻ ማእከል ያደረገ አዲስ የሊዝ ዋጋ እንዲዘጋጅ የሚያደርግ ሲሆን ከነበረው የመኖሪያ ቤት መነሻ የሊዝ ዋጋ ያነሰ መሆን አለበት።
- ለያንዳንዱ አባል ቦታ የሚፈቀድለት በአካባቢው ለማህበራት ተብሎ የተዘጋጀ መነሻ የሊዝ ዋጋ ይሆናል።
- የሊዝ ዋጋ መክፈል የሚጀምረው የግል ካርታ ለያዘ ሲሆን፤ ማህበሩ ቦታ ከተረከበበት ከስድስት ወር መብለጥ የለበትም።

- እያንዳንዱ የማህበሩ አባል የሊዝ ውል ሲፈፅም የቅድሚያ ክፍያ አስር በመቶ (10%) እንዲከፍል ይደረጋል፡፡
- እያንዳንዱ የማህበሩ አባል የግል ካርታ ከያዘ የሊዝ መሬት ስምምነት የሚፈፅሙ ሲሆን በሊዝ ደንቡ በተቀመጠው የሊዝ ዘመን ይሆናል፡፡
- የከተማው የመሬት ሊዝ ዘመን ማስላት የሚጀመረው ማህበራት ቦታ ከተረከቡበት ጊዜ ጀምሮ ሲሆን፣ ክፍያ የሚጀመረው ግን የግል ካርታ ከያዙበት ጊዜ ጀምሮ ሁኖ፣ በሊዝ መመሪያው በተጠቀሰው የመክፈያ ጊዜ ተሰልቶ ይሆናል፡፡

ሸ. ወደ ሦስተኛ ወገን ማስተላለፍና ለካፒታል ማስያዣነት መጠቀም፣

- ማንኛውም አባል ከውርስ በስተቀር ግንባታውን ሙሉ በሙሉ ሳይጠናቀቅ ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ አይችልም፡፡
- ማንኛውም ማህበር መሬት ከተረከበ ወይም ከመረከቡ በፊት በማህበሩ ስም በባንክ ወይም በማክሮፋናንስ በካፒታል መዋጮ ማስያዝ አይችልም፡፡
- እያንዳንዱ የማህበሩ አባል የግል ካርታ ከያዙ በኋላ ይዞታቸውን በካፒታል መዋጮ የማስያዝና ወደ ሦስተኛ ወገን የማስተላለፍ መብት ያላቸው ሲሆን፣ ግንባታው ተጠናቆ ከገቡበት በ5 (አምስት) ዓመት ውስጥ ወደ ሦስተኛ ወገን ካላስተላለፈ በዚህ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ፕሮግራም እና ሌሎች ተመሳሳይ ፕሮግራሞች እንዲሁም በመንግስት ቤቶች ፕሮግራም ተጠቃሚ መሆን አይችልም፡፡
- ማንኛውም የማህበሩ አባል ፕሮግራሙ የማይገባው ሁኖ ሲገኝ እና የመጠቀም መብቱ እንዲነጠቅ ሲወሰን፣ ማህበሩ ከአደራጀው አካል ጋር በመመካከር የሚተካው ሌላ አካል በዚህ የአደረጃጀት መመሪያ መሰረት ያሟላ ሲሆን ነው፡፡
- ማንኛውም ማህበር ግንባታው በውሉ መሰረት ካልጀመረ ወይም ካላጠናቀቀ በባንክ/ማይክሮፋይናንስ ከቆጠበው ገንዘብ አስር ከመቶ (10%) ሙሉ በሙሉ ወደ መንግስት ገቢ በማድረግ የተሰጠው ቦታ እንዲነጠቅ በማድረግ አሟልቶ ለቀረበ ሌላ ማህበር ይሰጣል፡፡
- ማህበሩ ግንባታ ጀምሮ በውሉ መሰረት ካላጠናቀቀ በሊዝ መመሪያው መሰረት የህንጻው ግምት ተሰልቶ መሬቱ አሟልቶ ለቀረበ ሌላ ማህበር እንዲዛወር ይደረጋል፡፡
- ማንኛውም ማህበር ከተፈቀደው ዲዛን እና ቦታ ውጪ ከገነባ በሊዝ አዋጅ እና የህንጻ አዋጅ መሰረት ቅጣት ተቀጥቶ ቦታው ገቢ ሊደረግ ይችላል፡፡

## ቅፅ - 001

## በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ ዋና የሥራ ሒደት

## የራስ አገዝ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ሕ/ስ/ማ ለመደራጀት መመዝገቢያ ማመልከቻ ቅፅ፣

ፎቶ

1.1 <u>የአመልካች ሁኔታ</u>

1.1. ስም፡----------------------------------- የአባት ስም ------------------------------
የአያት ስም ----------------------------------፣
ፆታ --------------   የትውልድ ዘመን /-----/-----/----- ዓ.ም

1.2. የእናት ስም፡ -------------------------------- የእናት አባት ስም፡ -----------------------------------
የእናት አያት ስም፡ ------------------------------------------

1.3. የትዳር ሁኔታ፡- ያገባ/ባች ☐ ያላገባ/ባች ☐ በፌች የተለየ/ች ☐ በሞት የተለየ/ች ☐
ያገባች ከሆነ የባለቤት ስም እስከ አያት -------------------------------------------------

1.4. የአመልካች የመኖሪያ አድራሻ
☐ ክፍለ ከተማ/ቀበሌ ----------------------------------------------------------------------
☐ የቤት ቁጥር ----------------------------------------- የነሪነት መታወቂያ ቁጥር -----------------
☐ የቤት ስልክ ቁጥር --------------------------------------- የሞባይል ቁጥር ----------------------

1.5. የሚኖርበት/የምትኖርበት ቤት ሁኔታ፡- የቀበሌ ☐ የኪራይ ቤቶች ☐ ደባል ☐ ጥገኛ ☐
የግለሰብ ኪራይ ☐ ሌላ ☐

1.6. አመልካች በከተማው በተከታታይ የኖረባቸው ዓመታት --------------------------

1.7. አመልካች የ ------------------------------------ ከተማ ነሪ ሆኖ ነገር ግን በተከታታይ ለሁለት ዓመት በሥራ ወይም በትምህርት ምክንያት ከከተማው ውጭ የኖረ መሆኑ ማስረጃ ካለው ይግለፅ፣

1.8. የሥራ ሁኔታ፡- የመንግስት ተቀጣሪ፡ ☐ የልማት ተቋም፣ ☐ የግል ሥራ ☐፣
ሌላ ካለ ☐

1.9. የሥራ አድራሻ

የመ/ቤት ስም ---------------------------------------------------------- የሚገኝበት --------------------

ክ/ከተማ/ቀበሌ ------------------------ ስልክ ቁጥር ---------------------------------------------------

ፖ.ሣ.ቁ፡------------------- ኢሜል ------------------------------

1.10 አመልካች የአካል ጉዳተኛ ነው ☐ አይደለም ☐

አካል ጉዳተኛ ከሆነ የጉዳት ዓይነት ማረጋገጫ ማስረጃ ይገለፅ --------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------

4.2 የ ----------------------------------------------- ማህበር ዝግ ሒሣብ የቁጠባ ደብተር ቁጥር ------------

ቅርንጫፍ ------------------------------

7. እኔ ስሜ ከላይ የተገለፀው አመልካች፡-

7.1 በ --------------------------- ከተማ ውስጥ በስሜ ወይም በትዳር ጓደኛዬ ስም የተመዘገበ መኖሪያ ቤት ወይም የቤት መሥሪያ ቦታ የሌለኝ መሆኑ፣

7.2 በ ---------------- ከተማ ውስጥ ቢያንስ ለተከታታይ 2 ዓመት የኖርኩ መሆኔን /በኗሪነት በሚደራጁ/

7.3 በዚህ የማመልከቻ ቅፅ የሞላሁትና ያስረከብኩት ማረጋገጫ ስህተት ሆኖ ከተገኘ የምዝገባ ወሉ የሚፈረስ መሆኑ የተሰጠኝ ሙብት ለሚመለከተው ለማግኘት በዚህ መመሪያ አንቀፅ 19 የተቀመጡትን ቅጣቶች በህጉ መሰረት ተጠያቂ እንደምሆን በመስማማት ይህን ማመልከቻ ቅፅ ዛሬ ------- ቀን -------- ዓ.ም የሞላሁኝ መሆኔ በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

**የአመልካች ስም፡ ------------------------------------- ፊርማ፡ -----------------------------------------**

